# በኛ ይብቃ!!

## በግንቦት 7 መሪዎች ተራ የውንብድናና የማታለል ተግባር ከደቡብ አፍሪካ ኤርትራ ሐሬና በረሃና ሱዳን መሬት ድረስ የዘለቀ አስከፊ የመከራና የስቃይ ታሪክ

### 1. *መንደርደሪያ*

የዚህ ማስታወሻ ፀሃፊ ከደቡብ አፍሪካ በግንቦት 7 ተመልምዬ በኤርትራ ሐሬና በረሃ ውስጥ የተሰጠውን ስልጠና በማጠናቀቅ ለስራ ወደ ድንበር አከባቢ ከተላኩሁ በኋላ በአገኘሁት ጠባብና አደገኛ አጋጣሚ ተጠቅሜ በመጥፋት በአሁኑ ወቅት ሱዳን መሬት ውስጥ እገኛለሁ፡፡ ከዚያ የሲኦል መሬት ላወጣኝ አምላክ ያለኝ ምስጋና በቃላት መግለፅ አልችልም፡፡ በፈጣሪ ድጋፍና እርዳታ ወጥቻለሁ፡፡ ከአሁን በኋላ ለአመታት ወደኖርኩበት የስደት ህይወት ለመመለስ የምችልበት እድልም ይኖረኛል ብዬ ተስፋ አደርጌያለሁ፡፡ ሆኖም በግንቦት 7 መሪዎች የቅጥፈት ወሬ ተታለው ኤርትራ የገቡና ከታሰሩበት ማምለጥ ያልቻሉ በርካታ ጓደኞቼ አሁንም በሐሬና በረሃ ውስጥ በስቃይ ላይ ናቸው፡፡ ከፍተኛ የሆነ የስልጣን ጥምና ጉጉት አናታቸው ላይ ወጥቶ ያሳበዳቸው የግንቦት 7 መሪዎች ይህንን ቅጣ ያጣ የስልጣን ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲሉ ምንም በማያውቁ ድሃ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ላይ ከፍተኛ በደልና ይቅር የማይባል ወንጀል እየፈፀሙ ነው፡፡ አሁንም ወጣቶችን እያታተለሉ ወደ ኤርትራ ሐሬና ለማስገባት ላይ ታች እያሉ ነው፡፡ ይህ በምስኪን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ላይ እየደረሰ ያለው መከራና ስቃይ ማብቃት አለበት፡፡ "ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ" ነውና በግንቦት 7 መሪዎች ተታልዬ በስደት ከምኖርበት ሃገር ከደቡብ አፍሪካ ተነስቼ ወደ ሐሬና በረሃ በመግባት እስከ ሱዳን መሬት ድረስ ያሰላፍኩት በቃላት ለመግለፅ የሚያስቸግር እጅግ የከበደ የስቃይና የመከራ ህይወት በሃገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሃገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲያውቀው ታሪኩን በአጭሩ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፡፡

### 2. ወደ ደቡብ አፍሪካ የተደረገ የስደት ጉዞ

የተወለድኩት፣ ያደግሁትና የ12ኛ ክፍል ት/ምህርቴን ያጠናቀቅኩት አዲስ አበባ ከተማ ቀበና ተብሎ በሚታወቀው አከባቢ ነው፡፡ ከአማራ ቤተሰብ የተወለድኩ ኢትዮጵያዊ ነኝ፡፡ በ1995 ማለትም ከአስር አመት በፊት የትውልድ ሃገሬ ኢትዮጵያን በመልቀቅ ወደ ደቡብ አፍሪካ በስደት የገባሁት በህጋዊ መንገድ ነበር፡፡ የሄድኩትም እንደ አብዛኛው የሃገሬ ወጣት የተሻለ ህይወትና ኑሮ ፍለጋ እንጂ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኔ በተለየ በወያኔ በደል ስለደረሰብኝ ነው ብዬ መዋሸትን አልፈልግም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ራሴንና ከአባቴ ጋር ከተለያየች በኋላ በስንት መከራ ያሳደገችኝ ድሃ እናቴን የምረዳባት በጊዜው ደህና ሊባል የሚችል እለታዊ ገቢም ነበረኝ፡፡ ደቡብ አፍሪካ ከገባሁ በኋላ ግን ህይወት እንደጠበቅኩት ለኔ የተመቸ አልሆነልኝም፡፡ በባዕድ ሃገር ብዙ ስቃይና መከራ ደረሰብኝ፡፡ ሰርቼ ባጠራቀምኩት ትንሽ ፍራንክ አነስተኛ የንግድ ስራ ለመጀመር ደፋ ቀና ስል እንቅስቃሴዬን በቅርብ ሲከታተሉ የነበሩ የደቡብ አፍሪካ ወሮበሎች ገንዘቤንና ንብረቴን ለመዝረፍ ሲሉ ሆድ እቃዬን በጩቤ ዘርግፈው ባደረሱብኝ ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳት ከአንድ ወር ተኩል የሞትና የህይወት ትግል በኋላ ራሴን በአንድ የደቡብ አፍሪካ ሆስፒታል ውስጥ አገኘሁት፡፡ ቁስሉ ትንሽ ከዳነልኝ በኋላ ከሆስፒታል ወጥቼ አገር ቤት ሳለሁ በነበረኝ ሙያ ህይወቴን እንደ አዲስ "ሀ" ብዬ መጀመር ግድ ሆነብኝ፡፡

መራራውን የስደት ህይወት እንደገና እንደ አዲስ በመጀመር ከማገኛት ከእጅ ወደ አፍ የሆነች በጣም አነስተኛ እለታዊ ገቢ በመቆጠብ ድሃ እናቴን ለመርዳት ደፋ ቀና በምልበት ሰዓት ከምሰራበት ቦታ የሚመላለስ አንድ ሙሉጌታ ከሚባል ኢትዮጵያዊ ጋር ተዋወቅሁ፡፡ መቼም በዚያ መራራ የስደት ህይወት ውስጥ የአገር ልጅ እንደ እንጀራ ይናፍቃልና ከሙሉጌታ ጋር ቀስ በቀስ እየተቀራረብን ከዚያም እየተግባባን መጣን፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ሙሉጌታ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ በርካታ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስላሉ በትርፍ ጊዜህ ለምን ተሳትፎ አታደርግም፣ ላንተም ጥሩ ነው ከብዙ ኢትዮጵያውንና የውጪ ዜጎች ጋር ለመተዋወቅ እድል ታገኛለህ የሚል ሃሳብ አቀረበልኝ፡፡ እኔም ብዙም ሳላቅማማ ሃሳቡን ተቀበልሁት፡፡ በዚሁም መሰረት እሱ ራሱ ሙሉጌታ በሊቀመንበርነት እና ማስረሻ የተባለ ሌላ ሰው በፀሃፊነት የሚመሩት ቤተ-ኢትዮጵያ በሚባል ድርጅት ውስጥ ገብቼ መሳተፍ ጀመረኩ፡፡ ቤተ-ኢትዮጵያ በሽፋን የተመሰረተ የግንቦት 7 የድጋፍ መዋቅር መሆኑ የገባኝ ግን ወድያውኑ ነበር፡፡ “የውሃ ሙላት እያሳሳቀ ይወስዳል” እንዲሉ እኔም ብዙም ሳይገባኝና ሳላስበው በግንቦት 7 ፖለቲካ ውስጥ ገብቼ መዳከር ጀመርኩ፡፡ በዚህ መሃል በ2004 እነ አርቲስ ታማኝ በየነ የተገኙበት በደቡብ አፍሪካ የተካሄደው የኢሳት የገቢ ማሰባሰቢያ መድረክ ከተጠናቀቀ በኋላ የዚህ ድርጅት አመራር አባላት እርስ በርስ ተካሰው መወነጃጀል ሲጀምሩ እኔም ቀድሞውኑ በደንብ ሳላውቀው የገባሁበት ህይወት ስለነበር ለምን አርፌ የስደት ኑሮዬን አልገፋም ከሚል ውሳኔ ደርሼ አባልነቴን ለማቋረጥ ማሰላሰል ጀመርኩ፡፡

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ሙሉጌታ በሌላ ጊዜ እንደገና ሌላ ሃሳብ ይዞ መጣ፡፡ ግንቦት 7 በአሁኑ ጊዜ ወደ አንድ ትልቅ የትግል ምዕራፍ እየተሸጋገረ ነው፣ ይህንን አዲስ ምዕራፍ በብቃት መምራት የሚችል የአመራር አቅም መገንባት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በየሃገሩ ከሚገኙ አባላቱ መካከል ጠንካራ የሚባሉትን እየመረጠ ወደ ውጪ ሃገር በመውሰድ ለማስተማርና ለማሰልጠን እንቅስቃሴ የጀመረ ስለሆነ ለምን የዚህ እድል ተጠቃሚ አትሆንም የሚል ሃሳብ አቀረበልኝ፡፡ እሺም እምቢም የሚል ምላሽ ሳልሰጠው ስልጠናው ግን የት ነው የሚሰጠው? የሚል ጥያቄ አቀረብኩለት፡፡ እሱም አሁን ባለው ሁኔታ ሌላ አገር ማድረግ ስለማይቻል ከዚህ ወደ ኤርትራ ከገባችሁ በኋላ ከኤርትራ መደበኛ የጉዞ ሰነድ ተዘጋጅቶላችሁ ስልጠናው ወደሚሰጠበት አገር ምናልባትም ወደ አውሮፓ ልትሄዱ ትሄዳላችሁ አለኝ፡፡ “ወደ ኤርትራ ከገባችሁ በኋላ ከዚያ ወደ አውሮፓ ትሄዳላችሁ” የሚለው አባባሉ ብዙም አልተዋጠልኝም፡፡ በንግግሩ እምነት እንዳላደረብኝ ከገፅታዬ ያነበበው ሙሉጌታ አይዞህ ምንም ችግር እኮ አይኖርም፣ እዛ ከደረስክ በኋላ ምናልባት የጠበቅከው ሁኔታ እንኳን ባይገጥምህ ወደዚሁ መመለስ ትችላለህ፣ ምንም የሚያሳስብህ ነገር የለም አለኝ፡፡ ቀጥሎም ብቻዬን እንዳልሆንኩና ሌሎችም ለተመሳሳይ የስልጠናና የአመራር ትምህርት በጥንቃቄ የተመረጡ አብረውኝ የሚሄዱ ሰዎች እንዳሉ በመግለፅ ሊያደፋፍረኝ ሞከረ፡፡ እሺም እምቢም የሚል ምላሽ ሳልሰጠው በዚሁ ተለያየን፡፡

በሌላ ቀን ወደምሰራበት ቦታ እንደገና ተመልሶ በመምጣት እኔ ጋ ሆኖ ስልክ በመደወል አንዳርጋቸው ፅጌ ከሚባል ሰው ጋር እንድንገናኝ አደረገ፡፡ አንዳርጋቸው ከፍተኛ የግንቦት 7 አመራር ነው ሲባል በወሬ ከመስማቴ በቀር በአካል ፈፅሞ አላውቀውም፡፡ ደርግ ከወደቀ በኋላ የወያኔ ሹመኛ ሆኖ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ምክትል ከንቲባ እንደነበር በኋላ የሰማሁ ቢሆንም በወቅቱ በጣም ትንሽ ልጅ ስለነበርኩ እሱን ለማወቅ የምችልበት ሁኔታ ላይ አልነበርኩም፡፡ ሙሉጌታ ስልኩን ሲያቀበለኝ አንዳርጋቸውም ስሜን ጠርቶ ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረበልኝ፡፡ ስለእኔ ማንነት ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ

እውቀት እንዳለው፣ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ በስራ ወዳድነታቸውና በስነምግባራቸው ከሚታወቁ ጥቂት ጠንካራ የሚባሉ የግንቦት 7 አባላት መካከል አንዱ እንደሆንኩና በዚህም ምክንያት ለዚሁ ድርጅቱን የመምራት ታላቅ ሃላፊነት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በከፍተኛ ጥንቃቄ ከተመረጡት ጥቂት አባላት መካከል አንዱ እንደሆንኩ ራሴን እስከምጠራጠር ድረስ ስለማንነቴ በሚያማልል ቋንቋ ገለፀልኝ፡፡ ይሁን እንጂ በጣም የቀዘቀዘና ግራ የተጋባ ምላሼን የተገነዘበው አንዳርጋቸው ልክ ሙሉጌታ እንዳለኝ "አይዞህ ከፍላጎታችሁ ውጪ እኮ ምንም የሚሆን ነገር የለም፣ እዚህ መጥታችሁ የጠበቃችሁት ነገር ሆኖ ካላገኛችሁት ወደ መጣችሁበት የመመለስ እድሉ አላችሁ" አለኝ፡፡ ውስጤ ሙሉ በሙሉ ባይቀበለውም ለጊዜው ለመገላገል ስል እሺ አልኩት፡፡ የኤሌክትሮኒክስ ትኬት እንደሚልክልኝ ነግሮኝ ተሰነባብተን ስልኩ ተዘጋ፡፡

በማግስቱ ሙሉጌታና ማስረሻ ከምሰራበት ቦታ መጥተው የጉዞ ሰነድና ትኬት ስለሚዘጋጅልህ የደቡብ አፍሪካ የስደተኞች መታወቂያ ወረቀትህንና 2 ጉርድ ፎቶግራፍ ስጠኝ፣ ማስረሻም ካንተ ጋር ስለሚሄድ ነው እግሬ መንገዴንም ይዥው የመጣሁት አለኝ፡፡ የጠየቀኝ የስደተኞች መታወቂያና ሁለት ጉርድ ፎቶግራፍ አዘጋጅቼ ሰጠሁት፡፡ ከተወሰነ ቀናት በኋላ ሁሉም ነገር ስላለቀ ለጉዞው እንድዘጋጅ በስልክ ከነገረኝ በኋላ ለበረራው አንድ ቀን ሲቀረው ሙሉጌታ አንድ ካፌ ቀጥሮኝ ስሄድ ሽታዬ፣ ወንድወሰን፣ ንጉሴ፣ ኮስሞስ፣ ቴዎድሮስና ማስረሻ የምንባል በደቡብ አፍሪካ ለምንኖር ስድስት ኢትዮጵያውያን የኤርትራ ሊሴ ፓሴ እንደተዘጋጀልን በማሳየት ሰነዱን ሳይሰጠን በበነጋታው ኤርፖርት እንድንገናኝ ቀጥሮ ሰጥቶን ተለያየን፡፡ በማግስቱ በቀጠሮው መሰረት ሁላችንም ኤርፖርት ተገናኘተን፡፡ ሙሉጌታ በየስማችን የተዘጋጀውን የኤርትራ ሊሴፓሴ፣ የግብፅ አየር መንገድ ትኬትና ለእያንዳንዳችን 2000 የደቡብ አፍሪካ ገንዘብ (ራንድ) ሰጥቶን መልካም መንገድ ይሁንላችሁ አይዟችሁ በርቱ እኔም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እከተላቻኋለሁ በማለት ተሰናብቶን ሄደ፡፡

## 3. ወደግብፅና ከዚያም ወደ አስመራ የተደረገ ጉዞ

ረቡዕ ጥቅምት 7 ቀን 2005 ምሽት ከደቡብ አፍሪካ በግብፅ አየር መንገድ ተሳፍረን ስድስታችን ግብፅ ካይሮ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ ደረስን፡፡ የአየር ትኬታችን በትራንዚት የተቆረጠ ስለነበረና መግቢያ ቪዛ ስላልነበረን ወደ ወደ ከተማ ለመግባት ብንጠይቅም በግብፅ የኢሚግሬሽን ባለስልጣናት ተከለከልን፡፡ በአይናችን እንቅልፍ የሚባል ነገር ሳይዞር ለ18 ሰዓታት ያህል እዚያው ካይሮ አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ለመቆየት ተገደድን፡፡ ከካይሮ እንደገና በሌላ የግብፅ የአየር መንገድ አርብ ምሽት ተነስተን ጥቅምት 10 ቀን 2005 ለቅዳሜ አጥቢያ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት አከባቢ ኤርትራ አስመራ አውሮፕላን ማረፊያ ደረስን፡፡

ከአውሮፕላኑ እንደወረድን አንድ የኤርትራ የሴኩሪቲ ባለስልጣን እና አንዳርጋቸው አውሮፕላኑ ካረፈበት ቦታ ላይ በመሆን ቆመው ሲጠብቁን ነበር፡፡ አንዳርጋቸው የሚባለው ሰው እሱ መሆኑን የነገረኝ ማስረሻ ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ያየሁት በዚሁ ሌሊት ነበር፡፡ ሁሉም መንገደኛ የሚገባበት የኢሚግሬሽን መቆጣጠሪያ ኬላ በመተው በአውቶብስ ተሳፍረን ወደ ቪአይፒ ሳሎን ገብተን ለአንድ ግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየን በኋላ በሚኒባስ ተሳፍረን ወደ አንድ ቪላ ቤት ገባን፡፡

አስመራ ከተማን ከዚህ በፊት ስለማላውቃት ያረፍንበት ቦታ በትክክል መግለፅ አልችልም፡፡ አጠገቡ "ፊያት" የሚል ራሱም የተሰቀለበት ህንፃም በጣም ያረጀ ትልቅ ታፔላ ተሰቅሎ ይታያል፡፡ ወደ ማረፊያ ቤቱ ስንገባ አንድ ከኬንያ የመጣ "አሰፋ" በሚል የኮድ ስም የተዋወቀን ሰው ከማግኘታችን በቀር ቤቱ

ውስጥ ሌላ ማንም ሰው አልነበረም፡፡ እዚያው ካደርን በኋላ በተመላላሽ ሰራተኝነት የተቀጠሩ ኤርትራውያን ሴቶች ቅዳሜ ጥዋት ጥቅምት 10 ቀን 2005 መጥተው ቁርስ እንድንበላ ካደረጉ በኋላ አንዳርጋቸው ሻይ ማኪያቶ ጠጡ እግረመንገዳችሁም ከተማውን እንድታዩት በማለት ካቴድራል ወደገኘው የታክሲዎች መናኸሪያ ይዞን ሄደ፡፡ ብዙም ሳንቆይ ወድያውኑ ተመልሰን የተዘጋጀልንን ምሳ በልተን ከቤቱ ሳንወጣ እዛው ውለን በዚያው አደርን፡፡ በማግስቱ እሁድ ጥቅምት 11 ቀን 2005 አንዳርጋቸው የኤርትራ ናቅፋ የሚባል ገንዘብ ሰጥቶን ሰው አይን ውስጥ እንዳትገቡ ሁለት ሁለት ብቻ እየሆናችሁ ከተማውን እየዞራችሁ ካያችሁ በኋላ በዚያውም ምሳችሁን ውጪ ብሉ ባለን መሰረት ከማረፊያ ቤቱ ወጥተን ከተማውን ስንዞር ዋልን፡፡ ሰኞ ቀንም በተመሳሳይ ሁኔታ አሳለፍን፡፡

አስመራ በቁሟ እየሞተች የምትገኝ አሳዛኝ ከተማ መሆኗን ለመታዘብ ረጅም ሰዓታት መዞርን አላስፈለገንም፡፡ በከተማው ውስጥ አዲስ የተሰራ ወይም የሚሰራ ህንፃ ፈፅሞ አይታይም፡፡ በጣልያን ዘመን የተሰሩ ጥንታዊ ህንፃዎቿ የግድግዳ ቀለማቸውና ልስናቸው በእርጅና እየተፈረካከሰ መውደቅና ግድግዳቸው መፍረስ ጀምረዋል፡፡ ህዝቡ የሚገኝበት አስከፊ የድህነት ህይወት ራሱ አፍ አውጥቶ ይናገራል፡፡ በእድሜ የገፉ ጧሪ ደጋፊ የሚሹ እናቶች የቆሸሸ ነጠላ ተከናንበው በየመንገዱ ቆሎና የባቄላ አሹቅ ይሸጣሉ፡፡ ወጣትና ጎልማሳ በሚባል የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰው መንገድ ላይ ለማየት ያስቸግራል፡፡ በህዝቡ ገፅታ ምንም አይነት ተስፋም ሆነ የተስፋ መንፈስ አይታይም፡፡ አስመራ ከተማ በደርግ የመጨረሻዎቹ የእድሜው ዘመናት በአስራዎቹ መጀመሪያ የእድሜ ክልል ላይ ሆኘ ከማስታውሰው የአዲስ አበባ ድባብና ትዕይንት ጋር በእጅጉ ተመሳሰለችብኝ፡፡ የከተማው ህይወት ፍፁም ካሰብኩት እና ከጠበቅኩሁት ውጪ ሆነብኝ፡፡ በእርግጥ ደቡብ አፍሪካ ለትምህርት ከተላኩ በኋላ ወደ ሃገራቸው አንመለስም ብለው እዚያው የቀሩ ኤርትራውያን ደንበኞቼ ወደምሰራበት ቦታ ሲመጡ በመጠኑም ቢሆንም ስለሃገራቸው ሁኔታ ሲያጫውቱኝ የነበረ ቢሆንም እንደዚህ ይሆናል ብዬ ግን በፍፁም አልገመትኩም፡፡ ሰኞ እለት ከጓደኛዬ ጋር ወደ አንዱ ካፌ ጎራ ብለን ማኪያቶ ስንጠጣ ኢትዮጵያውያንና አዲስ የመጣን እንግዶች መሆናችንን የተረዱ የካፌው አስተናጋጆች ለምን እንደመጣን ጠየቁን፡፡ እኛም ከኢትዮጵያ ሳይሆን ከሌላ ሃገር ለሽርሽር የመጣን ኢትዮጵያውያን መሆናችንን ስንነግራቸው “የሚታይ ሌላ አገር አጥቻችሁ ነው ወደዚህ የመጣችሁት” ብለው ተሳሳቁ፡፡ በመቀጠልም ከናንተ በፊት እዚህ የገቡት መውጪያ አጥተው የተወለዱበትን ቀን እየረገሙ ነው.... እያሉ ሲያጉተመትሙ አዳመጥናቸው፡፡ ማንነታችንን እና ለምን ጉዳይ እንደመጣንም በእርግጠኝነት እንዳወቁ ገባን፡፡

## 4. ወደ ሐሬና በረሃ የተደረገ ጉዞ

ማክሰኞ ጥቅምት 13 ቀን 2005 ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት አከባቢ ሻለቃ ሮቤል የሚባል አማርኛ ተናጋሪ የኤርትራ የፀጥታ ባለስልጣን አንድ ሬንጀር ወታደራዊ ተሽከርካሪ ይዞ በመምጣት ከአስመራ ተነስተን ከአንዳርጋቸውና ከአሰፋ ጋር በመሆን ጉዞ ወደ ሐሬና ማሰልጠኛ ጣቢያ ጀመርን፡፡ ከአስመራ ተነስተን አቁርደት ከተባለ ከተማ ውስጥ ቁርስ ከበላን በኋላ ተሰነይና ጉልጅ በሚባሉ ከተሞች በኩል አልፈን ከቀኑ 9 ሰዓት አከባቢ ሐሬና ደረስን፡፡ ሐሬና ከጥቂት የዳስ ቤቶች በቀር ውሃም ሆነ ልምላሜ ያልታደለ እልም ያለ ተራራማና ደረቅ ወንዝ የበዛበት በረሃ ነው፡፡ ሐሬና ስንደርስ ከተለያዩ ሃገራት በተለያየ መንገድ ተጉዘው ኤርትራ የገቡ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን አገኘን፡፡ እነዚህም

- ዘመነ ካሴ (የኮድ ስሙ በላይ ዘለቀ) ቀደም ሲል በባህርዳር የአማራ ክልል የኢህአዴግ ወጣቶች ሃላፊ የነበረና በ2004 ወደ ኬንያ ወጥቶ ከዚያም ወደ ኤርትራ የገባ፣ የግንቦት 7 ህዝባዊ ሀይል ተብሎ በተበተነው የፕሮፖጋንዳ ፎቶግራፍ ላይ ምስሉ ፊት ለፊት የሚታየው፣

- ከፍያለው (የኮድ ስሙ አሮን) የጎጃም መርዓዊ አከባቢ ተወላጅ ከዘመነ ካሴ ጋር በኬንያ በኩል ወደ ኤርትራ የገባ፣ ከፍተኛ የሆነ የማየት ችግር ያለበትና የልብ በሽተኛ የሆነ በዚህ ምክንያት ስልጠና ውስጥ ያልገባ፣
- ዜና ጉታ (የኮድ ስሙ ግርማቸው) ስዊዘርላንድ ከሚባል አገር እንደገባ ሲነገር የሰማሁት በአንድ ወቅት ስለ ግንቦት 7 ህዝባዊ ሀይል መመስረት እሱም እኛም እኩል በማናውቀው መንገድ በኢሳት መግለጫ ሲሰጥ የሰማነው፣ ከውቤ ጋር የተለየ ቀረቤታ ስለነበረው ከእንግሊዝ የመጣ ሰው ነው የሚሉም ነበሩ፣
- ሸዋንዳኝ (የኮድ ስሙ ዲያ ወይም ዲያስፖራ) ከአሜሪካን ሃገር ዳላስ ከሚባል ስቴት የገባና የሐሬና ኑሮ ያልጠበቀውና ያልተመቸው በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ራሱን መጣልና ብቻውን ማውራት የጀመረ፣
- ፋንታሁን አየነው (የኮድ ስሙ አስመላሽ) የደቡብ ጎንደር አከባቢ ተወላጅ በ2001 ከኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ከወጣ በኋላ በ2002 ኤርትራ የገባ፣ የአማራው ንቅናቄ ድርጅት መሪ ነው የሚባለው የኮ/ል አለሁበል አማረ ዘመድ ነኝ የሚል፣ አለሁበል የውጪ እድል አመቻችልሃለሁ ብሎ አታሎ ከሃገሬ እንድወጣ ካደረገኝ በኋላ በረሃ ላይ ጥሎኝ ጠፋ በማለት ሲያማርር የሰማሁት፣
- መሳፍንት አያሌው (የኮድ ስሙ ገበዬሁ) በቅርቡ ስዊድን ሃገር የገቡ ሚስቱንና አንድ ልጁን ጥሎ ባለፈው አመት ክረምት አከባቢ ወደ ኤርትራ ገብቶ ሰው ለመመልመል ሱዳን ሄዶ ነበር ሲባል የሰማሁትና ሐሬና ላይ የተቀላቀለን፣ የግንቦት 7 ህዝባዊ ሀይል ተብሎ በተበተነው ፎቶግራፍ ላይ ከዘመነ ካሴ ቀጥሎ የሚታየውና በስልጠናው ወቅት በሚሰነዝራቸው ግራ የሚያጋቡ አስተያየቶቹ በስፋት የሚታወቅ፣
- ዳኛቸው (ዳንኤል) ሱዳን ውስጥ ከሶስት አመት በላይ የቆየና አሁንም ሱዳን የሚመላለስ እንዲሁም
- ታጠቅ፣ መላኩና ደምሴ በሚባል የኮድ ስሞች የሚታወቁ ሌሎች ሶስት ሰዎች ደግሞ ከኢትዮጵያ በየጊዜው እየመጡ ተቀላቀሉን፣

በዚሁ መንገድ "የአመራር ስልጠና" ይሰጣቸኋል ተብለን ከተለያዩ ሃገራት ተመልምለን በተለያየ ጊዜና አቅጣጫ በኩል ወደ ኤርትራ የገባን ሰዎች በጠቅላላው 17 ደረስን፡፡ አንዳርጋቸው በወቅቱ ምንም ዝግጅት ስላልነበረው "የአለም ታላላቅ ህዝባዊ ትግሎች የሩቅ ራዕይና የአላማ ፅናት ባላቸው ጥቂት ቆራጥ የህዝብ ልጆች ተጀምረው በሂደት እየጎመሩ ለድል መብቃታቸውን" በየእለቱ ይተርክልናል፡፡ "ዘረኛው የወያኔ ቡድንም እኮ በ11 ሰው የካቲት 11 ቀን 1967 ደደቢት በረሃ ላይ የጀመረው የትጥቅ ትግል ነው ለድል የበቃው፣ ዋናው የዓላማ ፅናት ነው፣ ግንቦት 7 የትጥቅ ትግል መጀመሩ ወሬው አንድ ጊዜ ከተሰራጨ በወያኔ አገዛዝ ኩፉኛ የተማረረው ህዝባችን ሆ! ብሎ ይወጣል አትጠራጠሩ፣ በጣም የሚያሰጋን የወጣቱ ፍሰት አሁን መሸከም ከምንችለው አቅም በላይ እንዳይሆንብን ነው" እያለ ሲቀሰቅሰን ሰነበተ፡፡

ስልጠናውን በበላይነት የሚያስተባብሩ የግንቦት 7 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከውጪ ሃገር እስኪመጡ ድረስ አዲስ የሚመሰረተው የግንቦት 7 ወታደራዊ ድርጅት ህገደንብና መተዳደሪያ ላይ እየተወያየን እንጠብቃቸው በማለት ቀድሞ አዘጋጅቶት በጠበቀን ረቂቅ ፅሑፍ ላይ መወያየት ጀመርን፡፡ ከዚያም የግል ንብረታችንን በሙሉ ለድርጅቱ እንድናስረክብ መመርያ ሲያወርድ ከአባላት ከፍተኛ ተቃውሞ ተነሳ፡፡ በተለይ ከደቡብ አፍሪካና ከኬንያ የሄድን አባላት ከዚያ ስንነሳ የተነገረንና ኤርትራ ከገባን በኋላ ያጋጠመን ሁኔታ ፍፁም የማይጣጣምና የተነገረን በሙሉ ውሸት ስለሆነ በገባህልን ቃል መሰረት ወደመጣንበት እንድንመለስ ሁኔታዎችን አመቻችልን ብለን ወጥረን ያዝነው፡፡

አንዳርጋቸው ከጅምሩ ተቃውሞ ያስነሱትን አባላት ለማግባባትም ለማስፈራራትም ሞክሮ ሲያቅተው ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋና ከደቡብ አፍሪካ መልምሎ ከላከን ከሙሉጌታ ጋር በእስካይ ፒ እንድንገናኝ አደረገ፡፡ ብርሃኑ ነጋ በመካከላችሁ አለመግባባት ካለ በእልህና በቁጣ ሳይሆን በውይይት መፍታት መቻል አለባችሁ አለን፡፡ ቀጥሎም በጣም በሚገርም ተመሳሳይ የሆነ ቋንቋ "ከፍላጎታችሁ ውጪ የሚሆን ምንም ነገር የለም፣ እዚያው ለመቆየት ካልፈለጋችሁ መመለስ ትችላላችሁ፣ ከዚህ ውጪ ግን የምታመልኩበት መፅሐፍ ቁዱስን ጨምሮ የግል ንብረታችሁ እንድታስረክቡ መገደዳችሁ ግን ትክክል አይደለም፣ እኔም አላምንመበትም …ወዘተ" በማለት በተለመደው ጮሌ ምላሱ እኛን ለማረጋጋት ሞከረ፡፡

ከዚህ በኋላ አብዛኛው ሰው ሁኔታው ሁሉ ወዴት እያመራ እንደሆነ እና በግልፅ ተቃውሞ ቢያቀርብ ሻዕቢያ ሁሉንም ጠፍሮ በሚቆጣጠረው ሃገር ውስጥ ምን ዓይነት አደጋ ሊያጋጥመው እንደሚችል በሚገባ እየተረዳ ስለመጣ የሆዱን በሆዱ ይዞ ከሚቀራረበው ሰው ጋር ብቻ ምስጢሩን እያወራ ከዚያ በረሃ ማምለጥ የሚችልበትን አመቺ ጊዜና ሁኔታ ማሰብና ማሰላሰል ጀመረ፡፡

## 5. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከአውሮፓ ወደ ሐሬ መግባትና የስልጠናው መጀመር

ሁኔታዎች በእንዲህ እንዳሉ በህዳር ወር 2005 መጨረሻ አከባቢ የግንቦት 7 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የሆኑት ካሌብ (ከብራስለስ)፣ ዶ/ር ታደሰና ውቤ ከለንደን ተነስተው አንድ ላይ አስመራ ከገቡ በኋላ አንዳርጋቸው ወደ አስመራ በመሄድ በመኪና ይዘዋቸው ወደ ሐሬና መጣ፡፡ በአባላት ስለተነሳው ጥያቄ አስቀድሞ አውቀውት ይሁን መንገድ ላይ ተነግሮዋቸው ብቻ አይታወቅም አዲስ ከመጡት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በተለይ ከካሌብ ጋር የነበረው ግንኙነት በአጠቃላይ ከጅምሩ ፍፁም መደማመጥ የሌለበት እያንዳንዱ ቀን በንትርክና በጭቅጭቅ የተሞላ እጅግ የሚያስጠላ ህይወት እየሆነ መጣ፡፡

ስልጠናውን ከመጀመራችን በፊት እስከአሁን ድረስ ስለነበረ አጠቃላይ ሁኔታችን ግምገማ እናድርግ በሚል ሽፋን የተጀመረው ስብሰባም ገና ውይይቱ በቅጡ ሳይጀመር ካሌብ መድረኩን ተረክቦ "እዚህ የመጣችሁ አባላት ከፍተኛ የሆነ የዲስፕሊን ጉድለት እያሳያችሁ ነው" በማለት እኛን ለማስፈራራትና ለማሸማቀቅ ያደረገው ጥረት ስብሰባው ወደ ለየለት ፀብ እንዲያመራና ያለምንም ውጤት እንዲበተን አደረገው፡፡ ከዚያ በኋላ አባሉ የራሱን አማራጭ ለመውሰድ አመቺ ጊዜና ሁኔታ ከመጠበቅ በቀር ምንም አይነት ምርጫ እንደማይኖረው ገሃድ እየሆነለት መጣ፡፡ ይሁን እንጂ በየእለቱ ምግብ ተብሎ የሚቀርበው "ወዲ አከር" የሚባለው የማሽላ እንጀራና "አደስ" ብለው የሚጠሩት "ወጥ" ነው ለማለት እጅግ የሚያስቸግር ለብ ባለ ውሃ የተዘፈዘፈ የምስር ንፍሮ ኑሮአችንን ይበልጥ አከበደው፡፡

በዚህ አስከፊ የተስፋ መቁረጥ ህይወት ውስጥ እያለን ፖለቲካዊና ወታደራዊ ስልጠና ለመጀመር ዝግጅቱ እንደተጠናቀቀ ተነገረን፡፡ ዋናው ወታደራዊ ስልጠና እስኪጀመር ድረስም ከአውሮፓ የመጡት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በገቡ በሁለተኛው ቀን ዶ/ር ታደሰ ብሩ "እኔ ማነኝ፣ የሃገር ፍቅር ስሜት ማለት ምን ማለት ነው፣ ትዕግስት፣ አብሮነትና አብሮ መስራት (team spirit) ማለት ምን ማለት ነው" በሚሉ አርስቶች ዙርያ ኢትዮጵያዊነታችን አዲስ ግኝት እስኪመስለን ድረስ ስለሃገር መወድድና ስለኢትዮጵያዊነት እኛን ለመስበክ በከንቱ ሲደክም ሰነበተ፡፡

ዋናው ስልጠና የፈጀው 37 ቀናት ሲሆን የተጠናቀቀው ጥር 10 ቀን 2005 አከባቢ ነው፡፡ አሰፋ በሚባል የኮድ ስም የሚጠራው እና በኬንያ በኩል ገብቶ ቀድሞ አስመራ የጠበቀን የቀድሞ የደርግ ወታደር

የነበረው ሰው ጥዋት ጥዋት ስፖርት ያሰራናል፡፡ ቀን ደግሞ ባለው የውትድርና ልምድ የኤርትራ አሰልጣኞችን በመደገፍ ስራ ላይ ተሰማራ፡፡ ወታደራዊ ስልጠናውን የሰጡን ስሉስ፣ ሲሳይ እና ስህን በሚባሉ ስሞች የሚጠሩ የሻዕቢያ ወታደራዊና የስለላ መኮንኖች ሲሆኑ ስሉስ የሚባለው መሳርያ መፍታትና መግጠም፣ ደፈጣ፣ መመሳሰል፣ ምሽግ መስራት፣ ማጥቃት መከላከልና የእግር ጉዞ፣ ሲሳይ ወታደራዊ ሰልፍና አካሄድ፣ ስህን የተባለው ደግሞ ስለስለላ እና የጠላት ሁኔታ ማወቅ የሚሉ ትምህርቶች ሰጡን፡፡

እኛ ወታደራዊ ስልጠናውን ስንጀምር የግንቦት 7 ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ዋነኛ የስራ ድርሻ ወደ ማጀት ገብቶ ለሰልጣኞቹ የሚሆን ምግብ ማዘጋጀትና ማቅረብ ብቻ ሆነ፡፡ ስለእነዚህ ሰዎች እውነተኛ ማንነትና የወረደ ስብእና የኢትዮጵያ ህዝብ ማወቅ አለበት ብዬ ስለማምን ከእነዚህ ሰዎች ጋር በሐሬና በረሃ ለሶስት ወራት ያህል አብሬ በቆሁባቸው ጊዜያት ውስጥ ስለያንዳንዱ የስራ አስፈፃሚ አባል የታዘብኩትን ከዚህ በታች እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፡፡

- አንዳርጋቸው ፅጌ፡፡ ስልጠናውን በበላይነት የሚመራው እና ከኤርትራ ባለስልጣናት ጋር የሚገናኘው ብቸኛ ሰው ነው፡፡ ሃገር ማለት ምንድነው፣ ስለዜግነት፣ የዓላማ ፅናት የሚሉ አርዕስቶችን ይዞ የተወሰነ ቀን አስተምሮናል፡፡ ከእድሜው ጋር የማይመጥን የአካል እንቅስቃሴ በማድረግ ገና እንደሆነ ለማሳየት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የነበረ ቢሆንም እስከ ቅንድቡ ድረስ የወረረው ሽበቱና አካላዊ ብቃቱ የእድሜውን መግፋት ሊደብቁለት የሚችሉ አልነበረም፡፡ ሐሬና ከሳር በተሰራ ጎጆ ቤት ቁጭ ብሎ ሲፅፍና በስካይፒ ሲያወራ ይውላል፡፡ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ እንደታዘብኩት ከሆነ አንዳርጋቸው ፍፁም አምባገነን የሆነ ሰው ነው፡፡ አንተ በፍፁም መሪ መሆን አትችልም ብለን ያደምንበት ጊዜ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ያስገረመኝ አንዳርጋቸው ስለራሱ አውርቶ የማይሰለቸው ሰው መሆኑ ነው፡፡ በጣት ከሚቆጠሩት ከእነዚህ ሰልጣኞች እንኳን አድናቆታቸውን ከሚቸሩትና ከሚሰግዱለት ሰዎች ጋር የተለየ ቀረቤታን ለመፍጠር ሲሞክር አይቼዋለሁ፡፡ በአጠቃላይ አንዳርጋቸው የአባላትን ስሜት በመረዳትና ችግሮችን በመፍታት ድርጅትን መምራት የማይችል፣ ብቃት የሌለው ሰው ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡

- ካሌብ የድርጅቱ ምክትል ሊቀመንበር ነኝ የሚለው መቼም የሚገርም ሰው ነው፡፡ በግንቦት 7 ውስጥ በምን አይነት መለኪያ ለዚያ ስልጣን እንደበቃም ለመገመት በጣም ይከብደኛል፡፡ በሁሉም ሰልጣኞች ምንም አይነት ተቀባይነት ያልነበረው፣ የሚጨበጥ ባህርይ የሌለው፣ እንኳን ድርጅትን የሚያክል ነገር ሊመራ ቀርቶ እዚያ የተሰባሰብነው 17 ሰዎችን እንኳን እንደየባህርያችን መያዝና ማስተናገድ የማይችል በአወንታ የሚነሳ ምንም አይነት ጠንካራ ጎን የሌለው ደካማ ሰው ነው፡፡ የበታችነቱን ለመሸፈን ሲል ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ በከንቱ ሲደክም የሚታይ፣ እሱ ለሶስት ወር ብቻ የተለያቸው ሚስቱንና ልጆቹን በየቀኑ ወደ ቤልጅየም እየደወለ በስልክ ሲገናኝ ሌሎች አባላት ግን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለመገናኘት ጥረት ሲያደርጉ በዲስፕሊን ግድፈት ሲወነጅል የከረመ ደካማ ፍጥረት ነው፡፡ አንድ ቀን ከአባላት መካከል በስካይፒ ከወላጅ እናቱ ጋር ለመገናኘት ሙከራ ያደረገን አባል አበበ ቦጋለ ከሩቁ ተመልክቶ እጅግ በሚገርም ፍጥነት እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ማነጋገሪያውን (head set) ከልጁ ጭንቅላት መንጭቆ ሲነጥቀው የተመለከቱ ሌሎች ሰልጣኞች በአስመሳይ ባህርዩ እጅግ ተናደው ለመደብደብ የተነሱበት ጊዜም እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ በአጭሩ ካሌብ ማለት ለምንም አይነት ሃላፊነት የሚመጥን ብቃት የሌለው ደካማ ሰው ነው፡፡

- ዶ/ር ታደሰ ብሩ፡፡ የሚያሳዝን ተላላኪ ነው፡፡ በሌላ ሰው ጉድለት ጭቅጭቅ እንኳን ቢነሳ በማይመለከተው ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ራሱን ጥፋተኛ እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ እርቅ እንዲወርድ የሚታትርና ሁሉ ጊዜ "አሁን ስለ ችግሩ ትተን ወደ መፍትሔ እንሂድ" የሚል ሰው ነው፡፡ የፖለቲካ ስልጠናው የበላይ ሃላፊ ተብሎ የተመደበ ቢሆንም አንዳርጋቸውና ሌሎችን ሳያስፈቅድ መፀዳዳት አንኳን የማይችል በራሱ ላይ ምንም አይነት እምነት የሌለው ሰው ነው፡፡ እዛ በቆየበት ጊዜ በራሱ ውሳኔ የሚፈፅማቸው አንድም ነገር አላየሁም፡፡ የአስተማሪነት ችሎታውና ለስላሳ ባህርዬ ግን ለኛ ከሌሎች ሁሉ የተመቸ ሰው ነበር፡፡

- ብዙነህ ፅጌ፡፡ ብልጥ ነው፡፡ ሐሬና በቆየባቸው ጊዜያት መጀመሪያ የሰልጣኞች ሃላፊ በኋላ በነበረው አጭር ቆይታ ደግሞ የአባላት የምልመላ ሃላፊ ተብሎ ሲንቀሳቀስ ነበር፡፡ ሐሬና ውስጥ ውቤ የአንዳርጋቸው ታናሽ ወንድም መሆኑን የማያውቅ አባል አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ ወንድማማችነታቸው በግልፅ እንዳይታወቅ ያደርግ የነበረው ጥንቃቄ አስገራሚ ነበር፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በዝምታ ነው ያሳለፈው፡፡ ውቤ ኤርትራ ገብቶ በተመለከተውና በሚደረገው ነገር ሁሉ ከልቡ ደስተኛ እንዳልሆነ ከሁኔታው በቀላሉ መረዳት ይቻል ነበር፡፡ በተቅማጥ ህመምና መላ አካላቱ እያሳበጠ በሚፈነዳ በሽታ ተለክፎ መከራውን ሲያይ የከረመ ሰው ነው፡፡

## 6. የስልጠናው መጠናቀቅና የአመራር ምርጫ ተከትሎ የተፈጠረው ውዝግብ

ስልጠናው እንደነገሩ ተጠናቅቆ ኑሮአቸውን እዚያ ሐሬና በረሃ ያደረጉ የተቃዋሚ ቡድኖች አመራሮችና የሻዕቢያ ባለስልጣናት በተገኙበት የምረቃ ስነስርዓቱ ከተካሄደ በኋላ ለሶስት ወራት ጉብኝት የመጡት የግንቦት 7 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ወደየመጡበት ሃገር ከመመለሳቸው በፊት በተዘጋጀው መዋቅር መሰረት የአዲሱ የግንቦት 7 ህዝባዊ ሀይል አመራር ምርጫ መካሄድ አለበት ተባለና ስብሰባ ተቀመጥን፡፡

ምክንያቱን በግልፅ ባይነግሩንም የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴው አባላት በምርጫው ውስጥ እንደማይገቡ አስቀድመው ነገሩን፡፡ እውነታው ግን ከአባሉ የተሰወረ አልነበረም፡፡ እነሱ የውጪ ዜግነት ያላቸው ሰዎች ስለሆኑ ነገ ጥዋት ተነስተው ወደየመጡበት ሃገር እንደሚመለሱ ያውቃሉ፡፡ ስለዚህም ወታደራዊ እንቅስቃሴ ጀምሬያለሁ በማለት ጦርነት ባወጀ ድርጅት ውስጥ ስማቸውን ከተው ራሳቸውን "ለአሸባሪነት" ወንጀል አሳልፈው መስጠትን አይፈልጉም፡፡ እነሱ መሞት፣ መታሰር፣ መወንጀልን ሳይሆን የድሃው ኢትዮጵያዊ ልጅ ሞቶላቸው ስልጣን መያዝን ብቻ ነው የሚፈልጉት፡፡ አንዳርጋቸው ፅጌ በተዘጋጀው የግንቦት 7 ህዝባዊ ሀይል መዋቅር ውስጥ በአይን የማይታይ ሳጥን አበጅቶ ራሱን በአማካሪነት በመሰየም የአመራር ምርጫው ተጀመረ፡፡

ምርጫው ነፃና ዲሞክራሲያዊ መሆን አለበት ስለተባለም ፋንታሁን አየነው (አስመላሽ) እና ሽታዬ (ቼጎቬራ) የሚገኙበት ገለልተኛ አስመራጭ ኮሚቴ በአባላት ተመረጡ፡፡ በዚሁ መሰረት ምርጫው በምስጢር ተካሄዶ የምርጫ ውጤቱ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ፀድቆ ለአባላት እንዲገለፅ ሃላፊነቱን ለስራ አስፈፃሚው ተሰጠ፡፡

አስመራጭ ኮሚቴው መሳፍንት አያሌው (ገበዬሁ) በዋና አዛዥነት፣ አሰፋና ቴዴ (ምንሊክ) ደግሞ ሁለቱን በምክትል አዛዥነት መመረጣቸውን የሚያሳይ ውጤት ቢያቀርብም እነ አንዳርጋቸው ታማኝ አሽከሮቻቸውን መሾም ስለነበረባቸው ያለምንም ይሉኝታና ሃፍረት ውጤቱን ገልብጠው አሰፋ የተባለውን

በዋና አዛዥነት መላኩ በሚል የኮድ ስም የሚታወቀውን ደግሞ በምክትል አዛዥነት እንደተመረጡ አድርገው ሪፖርት ሲያቀርቡ ከፍተኛ ጭቅጭቅና ተቃወሞ ተነሳ፡፡

የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት የምርጫውን ውጤት ራሳቸው ለቤቱ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ በስራ አስፈፃሚው የቀረበው የምርጫ ውጤት ሪፖርት ትክክል እንዳልሆነ በማጋለጣቸው አባሉ ለሁለት ተከፍሎ ከፍተኛ ውዝግብ ተፈጠረ፡፡ “ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው” ነውና ቀድሞውኑ “አታለውና አጭበርበረው ኤርትራ አስገቡን” በሚል ከፍተኛ ቅሬታና ፀፀት ውስጥ ገብቶ የቆየው አብዛኛው አባል በዚህ አይነት ሁኔታ እዚህ ድርጅት ውስጥ መቀጠል አንፈልግም፣ ስለሆነም ወደየመጣንበት ሃገር መልሱን የሚል ጩኸት ማሰማት ጀመረ፡፡

ገና ከመግባቱ ከካሌብ ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ የገባውና ኤርትራ ከደረሰ በኋላ ያጋጠመው ሁኔታ የጠበቀው አይነት አለመሆኑ ሲገነዘብ ለምን መጣሁ? በሚል ቁጭት ብቻውን መናገርና ማሰብ የጀመረው ዘመነ ካሴ (በላይ ዘለቀ)፣ እግራቸው የኤርትራ መሬት ከረገጠበት ማግስት ጀምሮ ወደመጣንበት ሃገር ወደ ደቡብ አፍሪካ መልሱን በማለት ሲጠይቁ የነበሩ ማስረሻ (ዓባስ)፣ ቴዲ (ምኒሊክ)፣ ሽታዬ (ቼጎቬራ) እና ሌሎቹም ድርጅቱ እንዲያሰናብታቸው በፅሑፍ ማመልከቻ አቀረቡ፡፡ በተፈጠረው ሁኔታ የተደናገጡት ሶስቱ ቱሪስቶች (ካሌብ፣ ዶ/ር ታደሰና ውቤ) ውዝግቡ እስኪፈታ ድረስ እንኳን ትዕግስት ስላጡና አስቸጋሪው የሐሬና ህይወት መሸከም ከሚችሉት በላይ እየሆነባቸው ስለሄደ እኛን እዚያ በረሃ ውስጥ ጥለው ወደየመጡበት ሃገር እብስ ብለው ሔዱ፡፡

አንዳርጋቸው ቱሪስት ጓደኞቹን ወደመጡበት ሃገር ከሸኛቸው በኋላ ከአባላት ጋር የተፈጠረውን ችግር “እንዲፈቱለት” ኮረኔል ፍፁም ይሳቅ፣ ሻለቃ ዳዊት ዘርአይ፣ እና ሻለቃ ሮቤል የተባሉ የኤርትራ መንግስት ከፍተኛ የስለላ ባለስልጣናት የሆኑ የቅርብ አለቆቹን ይዞ ወደኛ ተመለሰ፡፡ እነ ኮረኔል ፍፁም ተራ በሆነ ሴራ ምክንያት ውዝግቡ እንደተፈጠረ ገብቷዋቸዋል፡፡ እናም የተፈጠረውን ችግር ከኛ ጋር ቁጭ ብለው በመወያየት ለመፍታት መምጣቸውን ከገለፁ በኋላ ቀጥለው “ከዚህ ውጪ የመጣችሁበትን ዓላማ ከግብ ሳታደርሱ ወደመጣንበት ሃገር መልሱን የሚለው ጥያቄ ግን ፍፁም የሚታሰብ አይደለም” በማለት እቅጩን ነገሩን፡፡ የኤርትራ መሬት ከረገጥንበት ጊዜ ጀምሮ የሻዕቢያ እስረኞች መሆናችንን ያወቅነው ቢሆንም የሻዕቢያ ቱባ የስለላ ባለስልጣናት ከኤርትራ መውጣት የሚባለው ነገር ፈፅሞ ህልም መሆኑን በራሳቸው አንደበት ሲያረጋግጡልን የባሰ ችግር እንዳይደርስብን ምቹ ሁኔታ እስኪፈጠርልን ድረስ የሆዳችንን በሆዳችን ይዘን አርፈን መቀመጥ እንዳለብን ገባን፡፡

ከዚያም የውዝግቡ ዋና መነሻ ወደ ሆነው ወደ ምርጫው ጉዳይ እንግባ ተብሎ የሻዕቢያ የመረጃ ባለስልጣናት ችግሩን ሳንፈታ ከዚህ ቦታ አንሄድም ብለው ሁለት ቀን ሙሉ አወያዩን፡፡ የአባሉ የከረረ መንፈስና ስሜት ከተረዱ በኋላ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያሳለፈው ውሳኔ ስህተት ያለበት ስለሆነ ምርጫው እኛው ባለንበት እንደገና መካሄድ አለበት ብለው ድጋሚ ምርጫ ተካሄደ፡፡ በዚሁ ምርጫም አሰፋ ዋና አዛዥ፣ ገበዬህ (መሳፍንት) ምክትል አዛዥ እና በላይ ዘለቀ (ዘመነ ካሴ) የፖለቲካ ሃላፊ በመሆን ምርጫውን አሸንፈዋል ተብሎ ተነገረን፡፡ ዋና ፍላጎታቸው አሰፋን በዋና አዛዥነት ማስመረጥ ስለነበረ በእነአንዳርጋቸው ቀሽም ሴራ ሳይሆን በሻዕቢያ የረቀቀ የደፈጣ ድርጅታዊ ስልት “ምርጫው በዲሞክራሲያዊ መንገድ” ተጠናቅቋል ተብሎ ከዚያ በኋላ የአባላት ስራ ሃላፊነት ድልድል እንዲደረግና ስምሪት እንዲካሄድ ተወሰነ፡፡

## 7. በመጨረሻም ወደ ሱዳን የተደረገ ጉዞ

ስብሰባው ከተጠናቀቀ በኋላ በተካሄደው የአባላት ድልድል መሰረት ድርጅት የተፈጠረ ለማስመሰል ያህል በሌለ መዋቅርና ድርጅት

- የአስተዳደርና ፋይናንስ ሃላፊ ሽታዬ (ቼጎቬራ)፣
- የትምህርትና ስልጠና ማስረሻ (ዓባስ)፣
- የመረጃና ደህንነት ዜና ጉታ (ግርማቸው)
- የምልመላ ስራው የድርጅቱ ቁልፍና ዋናኛው ስራ በመሆኑ በመሳፍንት (ገበዬሁ) አስተባባሪነት ቴዴ (ምኒሊክ) መላኩ፣ ደምስና ዳንኤል የሚባሉ አባላት ተመደበው ስራ ይጀምሩ ተባለ፡፡

ከዚህ ምደባና ድልድል በኋላ ከሐሬና በረሃ ወደ ድንበር አከባቢ ለመንቀሳቀስ እድሉን ያገኙ አባላት እየጠፉ ወደ ኢትዮጵያና ወደ ሱዳን መግባት ሲጀምሩ እኔም በተገኘው አጋጣሚ የሻዕቢያ ወታደሮች ከፍተኛ የሆነ የድንበር ላይ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በዘዴ በማለፍ አስቸጋሪውን በረሃ በእግሬ በማቆራረጥ ወደ ሱዳን ለመግባት እድል አገኘሁ፡፡

ከእኔ በፊት ወደ ኢትዮጵያና ወደ ሱዳን መሬት መግባታቸውን የማውቃቸው አባላት ሁኔታ ለደህንነታችን ስል ለጊዜው ስማቸውንና ሁኔታቸውን ከመግለፅ እቆጠባለሁ፡፡ የተወሰኑት ወደ ኢትዮጵያ በመግባት እጃቸውን ለወያኔ የሰጡ የቀሩት ደግሞ በፍርሃት ማንነታቸውን ደብቀው ወደ ቤተሰቦቻቸው ገብተው መኖር የጀመሩ እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ ወደ ሱዳን ለመግባት በምዘጋጅበት ጊዜ ከሱዳንና ከኢትዮጵያ በተመሳሳይ ማታለል የተመለመሉ ስድስት ወጣቶች በኡምሐጀር በኩል ወደ ሐሬና ሲገቡ እንደነበር አይቻለሁ፡፡ እኛ ከሐሬና በረሃ ጠፍተን ከወጣን በኋላ የሻዕቢያ የስለላ ሰዎች በቀሩት አባላት ላይ የሚያካሄዱት ጥበቃና ቁጥጥር የተጠናከረ መሆኑና ልጆቹ ከቁም እስር ያልተናነሰ ህይወት እየገፉ መሆናቸውን ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ያለፍላጎታቸው ከታገቱበት የሻዕቢያ እስር ቤት ፈጣሪ ነፃ እንዲያወጣቸው እፀልይላቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ የግንቦት 7 ወስላታና ቀጣፊ መሪዎች ድሃ ወጣት ኢትዮጵያውንን በማጭበርበርና በማታለል ወደ ኤርትራ መሬት በማሻገር የሚፈፅሙት ከፍተኛ በደልና ወንጀል በአፋጣኝ እንዲያቆሙ በሃገር ውስጥና በውጪ ሃገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ የሆነ ወገን ሁሉ በያለበት ሆኖ ድምፁን እንዲያሰማ በዚህ ፅሑፍ መልእክትዬን አስተላልፋለሁ፡፡

የደህነነቴ ጉዳይ አስተማማኝ እየሆነ ሲሆን በግንቦት 7 መሪዎችና በሻዕቢያ እጅ በኔና በጓደኞች ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለውን መከራና ስቃይ ወደፊት በአደባባይ ወጥቼ የምገልፀው ይሆናል፡፡

**ቴዎድሮስ ስዩም ሃይሌ (የኮድ ስም ምኒሊክ)**
**የግንቦት 7 ህዝባዊ ሀይል አባል**
**ከምድረ ሱዳን**